የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፲፯
አዲስ አበባ ጥር ፭ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 17
ADDIS ABABA-13th January,2004

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፫፻፹፪/፲፱፻፺፮ ዓ.ም

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ድርጅት ማቋቋሚያ /ማሻሻያ/ አዋጅ ........ ገጽ ፪ሺ፭፻፳፰

**CONTENTS**

Proclamation No. 382/2004

Ethiopian Agricultural Research Organization Establishment (Amendment) Proclamation ... Page 2528

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፹፪/፲፱፻፺፮

## የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ድርጅት ማቋቋሚያ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር ፫፻፹፪/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

፪. **ማሻሻያ**

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፸፱/፲፱፻፹፱ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፫ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ተተክቷል፤

"፪/ የድርጅቱ ተጠሪነት ለግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ይሆናል፤"

## PROCLAMATION NO.382/2004.

## A PROCLAMATION TO AMEND THE ETHIOPIA AGRICULTURAL RSEARCH ORGANIZATION ESTABLISHMENT PROCLAMATION

**WHEREAS**, it has become necessary to amend the Ethiopian Agricultural Research Organization Establishment Proclamation;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Ethiopian Agricultural Research Organization Establishment (Amendment) Proclamation No. 382/2004."

2. **Amendment**

The Ethiopian Agricultural Research Organization Establishment Proclamation No. 79/1997 is hereby amended as follows:

1/ Sub-Article (2) of Article 3 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (2):

"2/ The Organization shall be accountable to the Ministry of Agriculture and Rural Development."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ውስጥ "የግብርና ምርምር ቦርድ" የሚለው ስያሜ ተሰርዞ "የግብርና ምርምር አማካሪ ቦርድ" በሚለው ተተክቷል::

፫/ በአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ውስጥ "በቦርዱ አቅራቢነት" የሚለው ሐረግ ተሰርዟል::

፬/ የአዋጁ አንቀጽ ፱ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ /፱/ ተተክቷል፤

"፱/ <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ፣

፩/ በሚቀርቡ የግብርና የምርምር ሃሳቦች፣ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች እና

፪/ የድርጅቱን ዓላማ ለማሳካት በሚረዱ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ይመክራል፤ ሃሳብ ያቀርባል::"

፭/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ ፪ /ለ/፣ /ሐ/ እና /ረ/ ውስጥ "ቦርድ" የሚለው ተሠርዞ "የግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስቴር" በሚለው ተተክቷል::

፮/ በአዋጁ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ ፪ /ሠ/ ውስጥ "ቦርዱ በሚያፀድቀው መመሪያ መሠረት" የሚለው ሐረግ ተሠርዟል::

፫/ <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከጥር ፭ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ጥር ፭ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት



2/ The designation "Agricultural Research Board" under Sub-Article (1) of Article 7 of the Proclamation is deleted and replaced by the "Agricultural Research Advisory Board."

3/ The phrase "upon presentation by the Board" under Sub-Article (2) of Article 7 of the Proclamation is deleted.

4/ Article 9 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 9:

"9/ **<u>Powers and Duties of the Board</u>**

The Board shall deliberate and forward recommendation on:

1/ agricultural research proposals, programmes and projects; and

2/ other issues that contribute towards achieving the objectives of the Organization."

5/ The word "Board" under Sub-Article 2(b), (c) and (f) of Article 11 of the Proclamation is deleted and replaced by the "Ministry of Agriculture and Rural Development."

6/ The phrase "in accordance with the directives approved by the Board" under Sub-Article 2(e) of Article 11 of the Proclamation is deleted.

3. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the 13th day of January, 2004

**Done at Addis Ababa, this 13th day of January, 2004**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**